# ግልጽ ደብዳቤ ለወ/ሮ አዜብ መስፍን

*«... ደግሞስ ወደ መንግስት የመጣሽው እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆን ማን ያውቃል? » መጽ. አስቴር 4፥13-15*

*ይህንን ጦማር ለማዘጋጀት ያስገደዱኝ ዐበይት ቁም ነገሮች፡-*

1ኛ. በተለያየ ወቅት ስለ እርስዎ የምሰማው ነገር ሁሉ ምነው የልብ መካሪን የላቸውምን? የሚያሰኝ በመሆኑ፡ ነገሩ ሁሉ እየከፋ እንጂ እየተሻለው ሲሄድ ባለማየቴና ለከቡርነታቸው ደግሞ ትግሬ በነቂስ ወቶ ገመናቸውን ሲሸፍን በማየቴ ማናለበት ለንግስቲቱም እንዲህ በሰውም በመጣፍም ቢመክሯቸው ብዬ አንድም በመቆጨቴ አንድም ጥቃት ላለማስገባት በማሰቤ ነው።

በቃል እንዳላደርገው እርስዎ በየት ተገኝተው? በመልእክተኛ እንዳልሞክርዎት ይህን ደፍሮ የሚያደርስልኝ ሁነኛ ሰው ደግሞ አጣሁ።። አዳሜ ሁላ ለንጀራ ገመዷ ፈራች። ኣቦይ ስባት የሚባሉትም ቢሆኑ ኮከባቸው እንደ ማይዎድዎት አገሬው ሹክ አለኝ። እርስዎ ጠንቅቀው እንደሚያውቁት እርስዎ ጋር ለመገናኘት የቤተ-መንግስቱ በር ክፍት የተደረገላቸው በጣት ቢቆጠሩ አንድ እጅ እንኳን የማይሞሉት የተመረጡ ቤተ-ዘመዶችዎት ሁሉ ብላሽና ብሽቆች ናቸው።አንዳነዶቹ ባንድነት ከቤተሰቦችዎ ጋር የተነሱትን ምስል በማሳየት የሃገሪቱን ቦቅቧቃ ቱባና ዱባ ባለስልጣናትን ለማስፈራሪያና ያሻቸውን ያለገደብ ማስፈጠሚያ ሲያደርጉትና በባለሃብት ስም ከትራክተር እስከ ዘመናዊ ... ከቀረጥ ነጻ ማስገቢያ ዝቅ ሲል ደግሞ ለከተማ ቆነጃጅት ማባበያ ሲያውሉት አንዳንዶቹ ደግሞ ያለገደብ አይናቸው ያረፈበትን ግዙፍ የእርሻና የግንባታ ቦታ ሁሉ ከህግ ውጭ ባለይዞታውን መናጢ ደሃና ሌላውን መሰል ዘራፊ እያፈናቀሉ ከማግበስበስና ብሎም ተራና የተዛባ መረጃ ለወያኔ ገራፊዎች በማቀበል አበጀህ ኀበዜ ያላሏቸውን የቅርብ ዘመዶቻቸውን ጭምር ሳይቀር እንደ ለመዱት ከማሳሰርና ከማስገረፍ ውጭ ቁምነገር የላቸውም። ስለዚህ ሁነኛ መልእክተኛ አጥቸ እንዲሁ በሰረሰራየ ያለውን ሃሳብ ሁሉ ሳልገልጠው ሆድ ሆዴን እየበላኝ ከምቀር ማናልባት እንዲህ በዚህ በኩል የልቤን የወንድምነቴን ብመክርዎ ምናለበት በሚል።

2ኛ. ቀደም ሲል ንግስናዎ በደንብ እንዲህ ሳይደላደልና ሳይረጋ የወገናቸውን አቤቱታ አቤት የሚሉበት ቢያጡና ቢጨንቃቸው (እኔን ይጭነቀኝና) የትግሬው ገዥ ለነበሩት (አይ !ቀን ሲጥል) ለአቶ ገብሩ አስራት አቤት ብለው የነበሩቱ የሃገሬው ሽማግሌዎች እስከ ዛሬ ድረስ እንዲህ የደረሱበት ሳይታወቅ ደብዛቸው ጠፍቶ ሲቀርና ዛሬ እኔ ደርሽላቸው እነርሱን የወደቁበት ጉድባ ሁለ ገብቸ ማፈላለግ ቢቸግረኝም እንኳ  አቤቱታቸውን የማቀርብበት ቦታና እንዳው ኡኡኡ!!! የምልበት ደጅ ባጣ ፤እንዳው ፊደል ቆጥሬ ጡሁፍ ለመጣፍ ደርሽ መስሎኝ (ሙቀት ቢጤ ተሰማኝና)ማመልከቻ ወረቀት ማስገባበት ቦታ እርስዎ ዘንዳ ያገኘሁ ስለመሰለኝ።

3ኛ. ምናልባት እርስዎና ሰዎችዎ በተለይም ባለቤትዎ ማርክሲስት በመሆናችሁ የታላቁን መጽሐፍ ምክር ያላነበባችሁ/ያልተረዳችሁ ከሆነ በሚል እንደ አቅሚቲ እኔም ድሮ ልጅ ሳለሁ ከአባ ጎሃጽባሃ ኣፍ የሰማሁትን ባካፍልዎ መጣፉ እንደሚለው ብጠድቅ ብዬ።አዬ ጥድቅ እቴ።

(ይቅርታ ይደረግልኝና የተሸናፊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሳሙኤል ዘሸሬ የእርስዎ፤ አሸናፊው ሊቀ ጳጳስ አቡነ ጳውሎስ ዘአድዋ ደግሞ የክቡርነታቸው የንስሃ ይሁን ... ??? አባት እንደሆኑ ያኔ በ2001 ዓ.ም ክረምቱን ገደማ ሁለቱ በሚታገሉበት ወቅት

አሉባልታ ቢጤ ሰምቸ ነበር። ግና ዛዲያ ምናልባት እንዲህ ያለቸውን የጥድቅ ነገር ለመማማርና ለመመካከር ጊዜ አታገኙ እንደሆነ ብዬ በመጨነቄ ጭምር ነው።)

እንግዲህ ምክንያቴ ካጠገበዎት ያንብቡኝ፡ ካልተመቸዎት ግን ጥንቅር ብሎ ይቅር። ዋናው እርስዎ ደህና! ማስተዛዘን ልማዱ የሆነው ቀሪው ወገኔ ለማስተዛዘኛ/ለመዘባበቻ ያነበኛልና እንደ ተለመደው ባለማንበብዎት በጭራሽ አልከፋብዎትም። ይህም ሁሉ ባይሆንልኝ የተለመደው የሃገሬ ሎተሪ ላይ ማስተዛዘኛ እንኳ የማይዎጣለት እድሌ እዚህም ተከትሎኝ እንደመጣ ስለምረዳ ጣጣ የለውም።

እንግዲህ ጀመርኩ ይከተሉኝ!

መነሻ ታሪክ፡- መጽሐፈ አስቴር ከምዕ. 1-8

በአለም ታሪክ ብዙ ድንቅ ችሎታና ባህርያትን የተላበሱ ነገስታት እንደተነሱ መዛግብት ሲተርኩ ጥቂት የማይባሉ ንግስቶችንም አልዘነጓቸውም ። ከነዚህ መካከል ለዛሬ ጦማሬ ማነጣጠሪያ ትሆነኝ ዘንድ ታላቁና ቅዱሱ መጽሃፍ “መጽሐፍ ቅዱስ” እስከ ዘመናት ፍጻሜ የሚዘክራትን “ንግስት አስቴር”ን ላነሳሳት ወደድኩ። እነኋት አስቴር ዘአይሁድ በአጭሩ ከመጻሐፈ አስቴር እንደ ቀነጨብኳት፡-

ብልሁና ታላቁ አይሁዳዊ መርዶክዮስ ከእየሩሳሌም በምርኮ ተይዞ በታላቁ የአርጤክስስ ግዛት ስር በሱሳ ከተማ የአጎቱ የአሚናዳብን ልጅ አስቴርን ያሳድግ ነበር። ንጉስ አርጤክስስ በነገሰ በሶስተኛው አመት በሱሳ ከተማ የታላቁ የግርማዊነቱንም ክብሩንም ለ180 ቀናት ያህል ከግዛቱ ሁሉ ለተሰበሰቡት መኳንንት ካሳያቸው በኋላ ለመንግስቱ ክብር ባደረገው የ6ቀን ግበዣ ንጉሱ ስለተደሰተና ስለረካ በ7ኛውም ቀን ውብቷ እዺታይለት ንግስቲቱን የክብር ልብሷን አልብሰውና ዘውድ ጭነው እዲያመጧትና እንዲያነግሷት ንጉሱ አርጤክስስ ላገልጋዮቹ ባዘዘ ጊዜ ንግስት አስጢን የንጉሱን ትአዛዝ በመናቅ ወደ ንጉሱ መምጣትን እምቢ አለች።(አይ! ጌታ ሲጣላ)

ንጉስን ንቃለችና ንግስት አስጢንን በደስታው ድግስ መካከል ከክብሯና ከንግስትነቷ ካባረራት በኋላ እንደ ባለሚሎቹ ምክር በታላቁ የግዛት ክልሉ(ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ በተነንዘረጠጠው የ127 ሃገራት ዙፋኑ)ያሉ ምርጥ ደናግላን ሁሉ ተመርጠው በቤተ-መንግስቱ ለ 1 ዓመት ሲዋቡና ሲሽሞነሞኑ ከከረሙ በኋላ ነበር በየተራ ወደ ንጉሱ መኝታ የመጠራት እድል የሚሰጣቸው።

ታዲያ ይሄኔ ነበር መጻተኛዋ፣ እግዚአብሔርን በመፍራት፣ ባህሏንና ወጓን ጠብቃ፣ በስነ-ስርዓት በመርዶክዮስ እጅ ያደገችው መልከ መልካሟ አስቴር ለውድድር ከቀረቡት መንጋ ደናግላን መካከል የንጉሱ የአርጤክስስ ቀልብ ወደዳትና በታላቁ በአርጤክስስ ግዛት ሁሉ ንግስት ትሆን ዘንድ የተመረጠችው።

ውድ አንባቢዬ ! አስቴርን በአንድ ቀን አዳር ምን ብታደርግ ይሆን በንጉሱ ዘንድ ያስመረጣት ብለው እንደማይጠይቁኝ ተስፋ አደርጋለሁ።። ባይጠይቁኝም እወድ ነበር። ቢጠይቁኝም ግና መልሱን መስጠት የዚህ ጦማር አስኳል ነውና እነሆ በረከት፡-

አርጤክስስ በነገሰ በ12ኛው ዓመት፣ አስቴር በነገሰች በ6/7ኛው አመት በውድ አሳዳጊ አባቷ ላይ ገና ለገና ስወጣና ስገባ አልሰገደልኝም በኒል መርዶክዮስን ሊያጠፋው የተነሳው ፤ድሎትና ልቅነት ያሳበጠው የንጉሱ ቀኝ እጅ «ሐማ» በቅናት አይነ-ልቦናው ታውሮ ፣ በእብሪት እስከሞት ሰክሮ፤ ንጉሱ ያለገደብ የሰጠውን "ከሚስቴ በመለስ" አይነት ልቅ ስልጣኑን ተጠቅሞ አንድ መርዶክዮስን ለመጉዳት ሲል ብቻ በምርኮ በግዛቱ ሁሉ የተበተኑትን አይሁድን በተገኙበት ሁሉ ያለ ርህራሄ በአንድ ቀን ይጨፈጨፉ ዘንድ ፤ ንብረታቸውም ይዘረፍ ዘንድ ትእዛዝ በንጉሱ የቀለበት ማህተም በማተም በግዛቱ ሁሉ እንዲሰራጭ አስደረገ።

በምርኮና በድህነት ያደገችበትን ቤት ፍጹም በሚያስረሳ ድሎትና እንክብካቤ በንጉሱ ቤት የምትቀማጠለው ንግስት አስቴር ግን ከመንበሯ በወገኗና በህዝቧ ላይ የወጣውን የጥፋት ደብዳቤ በፍጹም አላወቀችም ነበር። ማንስ ነግሯት!። መርዶክዮስ እንዳዘዛት ማንነቷን ባለመግለጧ እርስዋ ከአይሁድ ወገን መሆኗንም ያወቀ አልነበረም።

ምን ያደርጋል "ነቅናቂ እያለ ማን ጥሩ ይጠጣል" እንዲሉ በሐማ እብደትና እብሪት የውድ አጎቷ አንገት ለአደባባይ ስቅላት፤ ወገኗ የእስራኤል ህዝብ ላይ ደግሞ መታረድ መታወጁን ደንገጡሮቿ መርዶውን በመንቀጥቀጥ ሹክ አሏት። ጃንደረባው አክራትዮስም ከመርዶክዮስ የተቀበለው የመርዶ ቃል እንዲህ የሚል ነበር፡-

"በእጄ እንዳደግሽ የችግርሽን ጊዜ አስቢ፤ከንጉሱ በታቸ የተሾመው ሐማ ይገድሉን ዘንድ አዟልና ወደ ጌታ ወደ እግዚአብሔር ለምኝ፤ ለንጉሱም ነግረሽ ከሞት አድኚን" መጽ. አስቴር 4፤8-9

አስቴርም ወደ ንጉሱ ሳልጠራ የገባሁ እንደሆነ የሞት ፍርድ እንደ ሚገባኝ አውቃለሁ በማለት ባቅማማች፣በፈራች እንዲህም ብላ መልእክት በላከችለት ጊዜ የመርዶክዮስን የመጨረሻው መልእክት እንዲህ ይነበባል፡-

"አንቺ በንጉስ ቤት ስለሆንሁ ከአይሁድ ሁሉ ተለይቸ ብቻየን እድናለሁ ብለሽ በልብሽ አታስቢ። በዚህ ጊዜ ቸል ብትይ ረድኤትና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ስፍራ ይሆንላቸል። አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ። ደግሞስ ወደ መንግስት የመጣሽው እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆነ ማን ያውቃል?" የሚል ነበር። መጽ. አስቴር 4፤13-15

ንግስትም የመረረውን የአባቷን ምክር በተቀበለች ጊዜ ወደ ልቦናዋ ተመለሰች፤ንግስናዋን ናቀች፤አላፊ ጠፊ መሆኗን አሰበች፤ከግል ምቾቷና ድሎቷ ባሻገር የህዝቧን የእስራኤልን ሀዘንና ሰቆቃ ተመለከተች። ዘሯ ከምድረ-ገጽ ጠፍቶ የእርሷ በዘሯ አጥፊዎች ሃገርና ቤተ-መንግስት በክብርና በንግስና መኖር ከንቱ የከንቱ ከንቱ መሆኑንና ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር በእርሷ ላይ ያለውን አላማ የተረዳች ሆነች። ለዚህም ያደረሳትንም እግዜአብሔርን በእውነት ፈራች።እንዲህም አደረገች፡-

እንደ አቅሟና እምነቷ ለእራሷና ለህዝቧ ጾምን አወጀች፤ የንግስና ልብሷንም ጥላ ማቅ ለብሳ ወደ አምላኳ ተንበረከከች፤ በሲሳ ከተማ ዙሪያ ያሉ ወገኖችም ሁሉ ለሶስት ቀን በመራራ ጾምና ጸሎት ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር እንዲጮሁ እንዲረዱትም አዘዘች፤እርሷም በባዕቷ ተወስና ከደንገጡሮቿ ጋር እንዲሁ አደረገች። ወደ ንጉሱም አልገባችም። (የአስቴርን ጸሎት በመጽ. አስቴር ምዕራፍ 4፤ ከቁ 17 ጀምሮ ይመልከቱ)

መለኛዋ ንግስት ቀድማ በጸሎት አምላከን ጠርታለችና በንጉሱ በአርጤክስ ፊት የሰጣትንም ሞገስ አስተውላለችና ንጉሱን ከሁሉ ለይታ ከወዳጁ ከሐማ ጋር ብቻ በቤቷ ጋበዘችው፤ በዘሯና በእርሷ ላይ በግፍ ሰይፉን፤ በአጎቷ ላይ ስቅላትን

ያወጀውን ሐማን ባልጠበቀውና ባልተዘጋጀበት መንገድ “ንጉስ በዙፋኑ ወንድ በሚስቱ … ነውና” ለንጉሱ ወዳጁ ሐማ በሚስቱም በመንግስቱም ላይ የመጣበት ቀበኛ አድርጋ በማሳጣት ንጉሱን በቅናት ጠልፋ ጣላቸው። ንጉሱም በሐማ ላይ እጅግ መራራ ቁጣን ተቆጣ። እዲህም ሆነ፡-

በወገኗ ላይ የወጣው የሞት ደብዳቤ ተሽሮ፤የዘሯ የእስራኤልንም ጥፋት በምህረት ውርደቱንም በክብር ተለውጦ፤ መርዶክዮስንም በክብር በሐማ ቦታ በንጉሱ ፊት ሞገስን አግኝቶ፤ ሐማም ለመርዶክዮስ መሰቀያ እራሱ ባዘጋጀው እንጨት ተሰቅሎ እንዲገደል ተደረገ።

በምርኮ፣በስደት፣በባእዳን ሀገር፣በንጉስ ቤት ከሃገሬው ቆነጃጅት አብልጦ ሞገስ የሰጣት እግዚአቤሔር ወገኖቹን የማዳን አላማ በእረሷ በኩል ሲከውን ለማየት በቃች። ለዚህም ክብር የመረጣትን አምላኳን አመሰገነች።

(በዚሁ አጋጣሚ የመጽሐፈ አስቴርን ሙሉውን ክፍል እንዲያነቡት በአክብሮት ጋብዣለሁ)

ውዷ ወ/ሮ አዜብ (ቀዳማዊት እመቤት)

ይኀው እርስዎ ንግስቲቱ … ገብቶዎትና ተገብቶዎት ወይም ሳይገባዎትና ሳይገባዎ በቅድመ አያቶችዎ በእነ ንግስት ጣይቱ ፣ በእነ እቴጌ መነን መንበር ነግሰው፤ በአሳዳጆቻችን በነ አቦ ለገሰ ቤተ-መንግስት ሞገስ አግኝተው እነሆ እኛ ኢትዮጵያውያን ወገኖችዎን በተለይ ደግሞ ተወልደው ያደጉበት የወልቃይት፣የአርማጭሆ፣ የጠገዴ፣ የሰቲት ሁመራ፣ የጠለምት የድፍን ጎንደር ህዝብ በምርኮ ተይዞ፤ ማንነታችን ተለውጦ፤ ትግሬ ሆነን የማናውቀውን ትግሬዎች ናችሁ ተብለን፤ተገደን የትግሬ ታርጋ ተለጥፎብን፤ ባህላችንና ማንነታችንን ተነጥቀን ትግሬነት ተጭኖብን፤ የመከራ ቀንበር ከብዶብን፤ ከቀያችን ተፈናቅለን፣ መሬታችንን ተነጥቀን፣ ያለደብራችን ተከልለን፣ ቅል-ቋንቁራችንን ተሸከመን ሀገር ላገር ተንከራተን፤ በየቀበሮ ጉድጓድ ታጉረን በየጉድባው ተገርፈን፣ ተገለን … ጎረ ስንቱ ይነገራል? ከአሳዳጆቻችን ጋር አብረው ሲያሳድዱንና እንዲህ ያለ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈጠምብን እነሆ 24/25 የመከራና የልቅሶ ዘመናትን እንዳያልፍ የለም አሳለፍን።

ምናልባት አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የአካባቢው ማህበረሰብ በተለየ ሁኔታ የከፈለውን መከራ፤የተጫነበትን የግፍ ቀንበር በትክክል ላይረዳው ይችል ይሆናል፤ ምናልባት በከፊል የአካባቢው ነዋሪ ትግርኛ ቋንቋ ስለሚናገር ወይም ስለአካባቢው ማህበረሰብ ትክክለኛው መረጃ ለሀገሬው ስላልደረሰውና ሁላችንም በደርግ የመከራ ቀንበር ስር ሰለነበርን ከደርግ መውደቅም በኃላ በትክክል የሆነውን ሁሉ ለመንግስት እግዚኦ እንዳንል የመከራው ዘመን ተጠናክሮ ስለቀጠለብን በተለይ ደግሞ በእኛ ላይ የሆነውንና የተደረገብንን ወገናችን ላያውቅልን ላይረዳው ወይም ላይሰማልን ይችል ይሆናል። ነገር ግን ለዘመናት እርስዎና ወራሪዎቻችን እንደምታውቁትበጎንደር ህዝብ ላይ፤በተለይ በወልቃይት፣በአርማጭሆ፣ በጠገዴ፣ በሰቲት ሁመራ፣ በጠለምት ማህበረሰብ ላይ የመከራው ዶፍ ይወርድብን የጀመረው ገና ከጅምሩ የደርግና የሌሎችም ድርጅቶች ደጋፊዎችና የታላቋ ትግራይ ምስረታ እንቅፋቶች ናችሁ/ይሆናሉ በሚል ቤተ-መንግስቱን ከመርገጣችሁ እጅግ በጣም ቀደም ብሎ ነበር።

(ውድ አንባቢዎቾ ምናልባት እግዚአብሄር የዛ ሰው ካለን በሌላ ጊዜ ወገናችሁ ከተሐት/ወያኔ ምስረታ እስከ ደርግ መውደቅ ድረስ ባለው ጊዜ ብቻ የታላቋ ትግራይ ምስረታ ትልቅ ስጋትና የደርግ/የኢዲዩ/የኢሃፓ ደጋፊና አባል ነው በሚል በወያኔ የደረሰበትን መከራ በሚቀጥለው ግዜ ለማንሳት እሞክራለሁ)

በአሁኑ ሰዓት በተጨባጭ እትብትዎ የተቀበረበት፣በፍቅርና በደስታ ቦርቀው ያደጉበት አካባቢ ታሪካዊ መጠሪያ ስሙን ተነጥቆ ከወልቃይት ወደ "ምእራብ ትግራይ" ከጠገዴ ወደ ...ምናምን...የመንደር ስሞች፣ የት/ቤት ስያሜዎች ሁሉ ሳይቀሩ ወደ ትግሬነት በመለወጥ "ሃውዜን 1ኛ ደ/ት/ቤት...ምናምን...ቅብጥርስዮ ..." ወዘተ ተብለው በትግሬያዊ ስሞች በመጥራት ታሪካዊ ስያሜያቸውን እንዲያጡ ሲደረጉ?

ባህሉ፣ወጉና ስርዓቱ በተለይ የሰርግ፣የለቅሶና የእድር የመሳሰሉት ግዙፎቹን የማህበራዊ ግንኙነቱን ሰንሰለቶች፤የማንነቱ መገለጫ የሆኑትን ባህላዊና ሀይማኖታዊ ስነ-ስርዓቶቹን ጥርትና ልቅም ባለ አማርኛ ቋንቋ ፤በጎንደርኛ ዘዬ እንደሚጠቀም እየታወቀ ልጆቹ በት/ቤት፣ አዋቂው በማንኛውም ማህበራዊ ግንኙነቱ፤ በየመንግስት የአገልግሎት መስጫ ተቋማቱ ሁሉ በትግርኛ ቋንቋ ብቻ እንዲጠቀም ... ለአለፉት 19 አመታት በመንግስት ደረጃ ታውጆበት ሲገደድ?

ያ! ኩሩ ኢትዮጵያዊ፣ ያ! ጀግና ህዝብ፤ ገና ገና ዱሮ የአርማጭሆን መሬት፣ የወልቃይትን መሬት፣የሰቲት ሁመራን፣ የመተማን፣ የዳንሻን፣ የአብደራፊን ... መሬት በበሬ ሳይሆን በትራክተር የሚያገላብጥ፤

ማረሻው ምንሽር መጎልጎያው ዳንዴ፣

ሰሜን አርማጭሆ ወልቃይት ጠገዴ፤ ... ተብሎ የተዘፈነለት ዘርዎ

አያቶቻችን፣አባቶቻችን የሀገራቸውን ዳር ድንበር ሳያስደፍሩ በየጋራው በየሸንተረሩ ደማቸውን ያፈሰሱቱ፣ አጥንታቸውን የከሰከሱቱ ፤ ከእነርሱ አብራክ የተወለዱት ልጆቹ ሳይነጥፉ መሬቱን በማናለብኝነት በሱዳን፣በባለ ጊዜ በትግሬ፣ በስመ ባለሃብትና በስመ ሰፋሪ ተነጥቆ ሲፈናቀል?

ህዝብዎ፤ የእናት አባትዎ ቤት ተራቁቶ፣ አብሮ አደግ ጓደኞችዎና ወገንዎ ህይዎታቸውን ለማትረፍ በየአቅጣጫው ሰብሳቢ አጥተው ተበትነው፤ ቀያችንን አንለቅም ብለውና እንዲሁም አቅም አጥተው የቀሩ ቤተሰቦች ኮሮዶቻቸው በግዳጅ በጋጠዎጥ የትግሬ አባዎራዎችና ጎረምሶች ሆን ተብሎ በተቀናበረ ሴራ ተደፍረው የትግሬ ዲቃላ ህጻናትን እንዲታቀፉ ሲገደዱ? (በአሁኑ ሰዓት በዚህ አመት ብቻ ከ82 በላይ ህጻናት በዚሁ ሁኔታ ተወልደዋል)

( በጨዋታችን ላይ፤ ቀደም ሲል የሰማሁት ሃሜታ እርስዎ የተገላቢጦሽ ለባለ ቅንድባሙ መሪያችን ጋብቻ በጥሎሽ መልክ መሬታችንን እንጂ ለተከታዮቻቸው ሴቶቻችንን ጭምር ጥሎሽ እንደሰጡ አልሰማሁም ነበር። ለካስ ነገሩ እንዲያ ኖሯል። ለማንኛውም ይህቺን ሃሜታ ሌላ ጊዜ እመለስባታለሁ። ቸር ይግጠመን እንጂ እንዲህ ሆድ ሆዴን ስትበላኝ አትኖርም።)

ያ! የወገንዎ ያ! የሚያውቁት የአራሾቹ፤ የጀግኖቹ የነ ኪዱ ቦጋለ፣የነ ባሻ መዓዛ መሬት፤ የነ ቀ/ኛ አያልነህ፣ የነ ሃይሌ ገ/ስላሴ ሀገር፤ የነ ደጃ ደስታ መሩ፣ የነ ቀኛ ሲሳይ አበራ ባድማ፤ የትላንቶቹ የነ መኩርያ ሃይሌ፣ የወጣቶቹ የነ ወልዴ የኔሁን፣ የነ አዲሴ ልጃለም ሀገር ... የዛ ሁሉ ጀግና የዛ ሁሉ ጎበዛ ሀገርና ድንበር እንዲህ በእርስዎ የንግስና ዘመን ሲፈታ? ኃረ ስንቱን ልዘርዝርልዎ? ይህ የመጣፊያ ቀለምና ወረቀት ከመካከል አቋረጦኝ ጉድ እንዳያደርገኝ እንጂ መንጋ ነበር ጨዋታዬ ...

እስኪ እንዳው አንድ ነገር ልጨምር ወቸ ጉድ! እንዳገሬው ሰው እየተመላለስኩ ሳወጋ እንዳላድር እንጂ????

እንዲህ ነው ! በተለይ በአሁኑ ሰአት ወገንዎ ከወያኔ የዘር ማጥፋት ፈርጀ ብዙና መጠነ ሰፊ ጥቃት፣ ከሞት፣ ከስደትና ጫካ ገብቶ ከጠላቱ ጋር ከሚፋለመው ወገኑ የተረፈውን ቀሪ ዘሩን ለማትረፍ ቀየውን ለትግሬ ሰፋሪዎችና ለዘመኑ ባለሃብት ተብዬዎች አስረክቦ/ተነጥቆ ጎንደር ከተማ ገብቶ ጎንደሬነቱን የሙጥኝ ብሎ ሲገኝ። በአንጻሩ የሚገርመው ደግሞ እርስዎና ግቢዎችዎ /ትግሬዎቹ/ ትግሬ ነህ ብትሉትም አንድም ወልቃይቴ ለአመል ያህል እንኳን ወደ መናገሻ ከተማችሁ /መቀሌ/ ይሁን ወደ ቀሪው የትግሬ ግዛት ቤተሰቡን ይዞ ለኑሮ ዝር ሳይል ሲቀር፤ እስኪ አንዴ ልጠይቅዎና ምን ተሰምቶዎት ይሆን? እንዳዉ በሞቴ ፤ አፈር ስሆን ሳይዋሹ (ደስታዎንትም ቢሆን) ይንገሩኝ።

ስለዚህ ውዷ ቀዳማዊት......

ከላይ በመጠኑም ቢሆን ዓበይት የንግስት አስቴርን የታሪክ ክፍሎች ለማንሳት ሞክሪያለሁ። ከእርስዎም ታሪክ ጋርም ባይሆን በመጠኑም ቢሆን ከእኛ ጋር ተመሳሳይነት አይቸበታለሁ።ልዩነቱ እደተጠበቀ ሆኖ ማለቴ ነው። ለምሳሌ ያህል ወደ በረሀ ከመውጣትዎ በፊት በተማሪነትዎ ዘመን በአጎቶችዎ ቤት በማደግዎ አሳዳጊዎ ማንነትዎን ጥቂትም ቢሆን ሳያስጠኑዎ አይቀሩምና (አጎትዎ የነ ደጃ ካሳ መሸሻ ቴዎድሮስ የቅርብ ወዳጅ እንደነበሩ አውቃለሁ) ፤ በጠላቶችዎ ቤተ-መንግስት ለንግስትነት መብቃትዎ ፤ በቤተ-መንግስትዎ ዘርዎን ለማጥፋት አዋጅ መውጣቱ ፤ ወገኖችዎ በሃዘን ፤ በፍርሃትና በመቅበዝበዝ ውስጥ መሆናቸው ፤ ይነስም ይብዛም ይህን የጠፋት አዋጅ ለመቀልበስ አቅም/መላ አያንስዎትም ብዬ በመገመቴ ፤ ... ወዘተ

እንዲሁም ደግሞ ታላቁ መርዶኪዎስ ለንግስት አስቴር " ... ደግሞስ ወደ መንግስት የመጣሽው እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆነ ማን ያዉቃል?" እንዳላት፡-

እርሷም ምክሩን አዳምጣ ወገኗን እስራኤልን ከጥፋት እንደታደገቻቸው ፤ እግዚአብሔርም አምላክም በጠላቶቿ ሀገር ሞገስ እንደሰጣትና ይህንንም ጸጋ በትጋት እንደተጠቀመችበት ፤ ትግሏንም እንደተወጣችው እንደ ንግስት አስቴር ፤ ማን ያውቅል በታሪክ አጋጣሚ ይሁን ወይ እግዚአብሔር በህዝቡ ላይ ባለው ድንቅ የማዳን አላማ ለጊዜው ባይገለጥልዎትም እህታችንን ዛሬ በገዛ ሀገራችን መጻተኞች ለሆነው ለእኛ ፤በቅኝ ገዥዎቻችን ቤተ - መንግስትና በወራሪዎቻችን መንደር ውስጥ ሞገስ ሰጥቶ ንግስት የመሆን እድል ያጎናጸፈዎት ወገንዎን ከጠላቶቹ እጅ እንዲታደጉ ፤ ዘርዎን ከጥፋት እንዲታደጉ ፤ ይሆን ይሆናል ብዬ ስለማስብ። ( ይህ ለዛሬ ሁላችንም እየኖርንበትና ለነገ ደግሞ ታሪክ የሚዘግበው የኢትዮጵያችን አብሻቂው ገጽታ ይሆን እንዴ?)

በድጋሚ ታላቁ መርዶኪዎስ ለንግስት አስቴር ፡-

"አንቺ በንጉስ ቤት ስለሆንሁ ከአይሁድ ሁሉ ተለይቸ ብቻየን እድናለሁ ብለሽ በልብሽ ብታስቢ፣ በዚህ ጊዜ ቸል ብትይ ረድኤትና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ስፍራ ይሆንላቸል። አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ። ደግሞስ ወደ መንግስት የመጣሽው እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆነ ማን ያውቃል?" መጽ አስቴር 4፤13-15 በማለት አበክሮ እንዳሳሰባት ሁሉ

ምን አልባት ይህን እድል እርስዎ ባይጠቀሙበትና ባያስተውሉትም እግዚአብሔር አምላክ የሚያስነሳው፣ ሞገስና ሃይል የሚያጎናጽፈው ብርቱ ሰው እንደሚመጣ በእምነት ሆኘ በሙሉ ልቤ ላረጋግጥልዎት እወዳለሁ። እንኳንስ አሁን ወገኖችዎ እንዲህ በአለም ሙሉ ተበትነን ይቅርና እዛው መንደራችን ወይ "ቀብቲሃ"ን ወይ "ጫቆ"ን አጥረው ሊያጠፉን ቢሞክሩም

ሃይልን የሚሰጠንን እግዚአብሔርንና ኩሩውን ወገናችንን የኢትዮጵያን ህዝብ ይዘን ጠላቶቻችንን ወደ መጡበት አሳፍረን በድል መመለሳችን የማይቀር ሃቅ በመሆኑና፤

ከሁሉም በላይ አሁን ወገንዎን የሚታደጉበት የእርስዎ ጀንበር እየጠለቀች መሆንዋ ስለተሰማኝ፡፡ ዘመንዎ ቢበዛ 5 ዓመት አልያም ግፋ ቢል 10 ዓመት ቢሆን ስለመሰለኝ፡፡ ያም በሰላም ቤተ-መንግስቱን ሌላዋ የወያኔ ንግስት ሳታስለቅቅዎ መሆኑ ነው፡፡ ወቸ ጉድ ! እረስቸው ወይ እርስዎ በተራዎ የመጀመሪያዋ እንስት ጠ/ሚ ጌታው ደግሞ በተራቸው ወደ ቀዳማዊ ጌትነት ወይ ወደ ኤፈርት … ሆናችሁ እዛው እንደ ልማዳችሁ ቤተ-መንግስቱን ካልባጃችሁበት በስተቀር … ወዘተ

እኔም የምር የወንድምነቴን/የልጅነቴን ላሳስብዎ ወደድኩ

ስለዚህ ክብርት ሆይ!

በመጨረሻም በአንድ ወቅት ባለቤትዎ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ጠንቋዮች ሰብስበው ስለ ማያልቀውና ስለ ማይ … የ5ቱ ግብርና መር/መራር … ፕላን/ትራንስፎርሜሽን በሚያወያዩበት ጊዜ አንድ ቀጠን ቀላ ያለ መምህር የሰጣቸውን የየዋህ ምክር (እራሱ ሰውዬው እንዳለው) እኔም ለዛሬ የዋህ ልሁንና ዛሬ ለእርስዎ ልድገመው …

እንዲህም ብዬ !

የሃገርዎን የታላቋን የኢትዮጵያን ህዝብ፤ የጀግናውን የጎንደርን ህዝብ፤የአርማጭሆን ህዝብ፤የወልቃይትን፣የጠገዴን፣ የሰቲት ሁመራን፣ የጠለምትን ህዝብ … ከወራሪዎቹ የሞት አዋጅ የመታደግ እድል በእጅዎ ነውና እድሉን እባክዎ ከመባከኑ በፊት አደራ በሰማይ አደራ በምድር ይጠቀሙበት እላለሁ!!!!!!

(ምናልባት ለክቡርነትዎና ለመንግስትዎ የማይመጥን ነገር ተናግሬ ከሆነ የጨዋ ነገር ሆኖብኝ ባለማወቅ ተሳስቶኝ ነውና በቅድሚያ ይቅርታ ይደረግልኝ)

ከአክብሮት ሰላምታና ምስጋና ጋር

አብዩ በለው ጌታሁን (abiyuye@gmail.com)

መስከረም/2003 ዓ.ም

ኦሃዮ/አሜሪካ